በፕሮፌሰር ቫጊፍ ፒርዬቭ
በታሪክ ፒ.ኤች.ዲ

# ካራባኽ - የአዛርባጃን ነፍስ

ሹሻ በር። 18ኛው ክ/ዘ።በ20ኛው ክፍለዘመን የ80 ዓመት ፎቶ የነበረና አሁን በአርሜኒያ የታጠቁ ኃይሎች ቁጥጥር ስር ያለ ከተማ



ካራባኽ 13ኛውንና 14ኛውን መቶ ክፍለ ዘመንን ጨምሮ በታሪክ የአዛርባጃን ግዛት ያልሆነችበት ዘመን የለም፡፡ ዝነኛው ሩሲያዊ የምስራቁ አለም ታሪክ አዋቂ ኤ ዋይ ያኩቦቭስኪ በትክክል እንደገለጸው፤ በጊዜው አዛርባጃን ማለት የአሁኑ የደቡብ ግዛት (ኢራን) እንዲሁም ሰሜን /የቀድሞ ሶቪየት/ አዛርባጃን ናቸው፡፡ ድንበሩም ከዛንጃን ወደ ደርቤትና ከጎይቻ ሃይቅ /የአሁኑ ሰቫን/ እስከ ካስፒያን ባህር ይደርስ ነበር፡፡ የቱሪስት መዳረሻ የሆነችው አዛርባጃን በአራት ግዛቶች የተከፋፈለች ነበረች፡፡ እነሱም ቱሁር ሳዓድ፣ ጋንጃ /ካራባኽ /፣ ጣብሪዝና ሺርቫን ናቸው፡፡ በወቅቱ ካራባኽ ታሪካዊዋች አራንን መሰረተች። እንዲሁም አራን የካራባኽ ማዕከልና ነብስ ነበረች። ቀዳሚ የእውነተኛ መረጃ የሚገኝባትም ሆነች፡፡

ካራባኽ የአዛርባጃን ግዛት ብቻም አልነበረችም። በካርስ (የኤስያ አነስተኛ ግዛት)፣ ሰሜን ኮካሰስ፣ ቱርክሚኒስታን፣ ኡዝበኪስታን፣ አፍጋኒስታንና የሌሎች አካልም ነበረች። በአዛርባጃን ሱርካብ ካራባኽ ፣ ጣብሪዝ ካራባኽ ና ካራባኽ



ጳደይ እና ሹሻ ውስጥ ያለው መስጊድ። በ18ኛው ክ/ዘመን የነበረ ዛሬ ግን በወራሪዎች የወደሙ



የካውካሺያን አልባኒያ/13ኛው ክ/ዘ የነበረ  ካራባኽ ውስጥ የሚገኘው ጋንድዛሳር ገዳም።
በአሁኑ ሰዓት ግን እንደገና ተገንብቶ የአርሜኒያ ገዳም የተባለ



አራን ተብለው የሚጠሩ አካባቢዎች ጭምር ነበሩ፡፡ ካራባኽ አራን ማለት ህዝብና የአትክልት ቦታ፣ ትልቁ የአትክልት ቦታና ተመራጭ መሬት እንዲሁም የመሬቱ ውበትና ብልጽግናው የሚታይበት ማለት ነው፡፡ የታሪክ ተመራማሪው አል ቁጥቢ አል አካሪ 14 ክ/ዘመን) ካራባኽ ን የአራን ርእሰ ከተማ ብሎ ጠርቷት ነበር፡፡

ከመካከለኛው ዘመን በኋላ እንደሚታወቀውም አራን በቁራና አራዝ ወንዞች መካከል ያለውን የመሬት ስፋት የሚሸፍን ነው፡፡ በዚህም የአራን ካራባኽ  ስም ከሌላኛው ካራባኽ  በተለይ በምስራቅ ካስፒያን ከምትገኝ ከባጂስ ካራባኽ ጋር ያለው ልዩነት ለማሳየት ተጠቅመውበታል፡፡

እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ናጎርኖ (ተራራማ) ካራባኽ በመካከለኛው ዘመን የታሪክ ጸሓፊዎች በተለይ በ13 - 14ኛ ክ/ዘመን ላይ አለመካተቱ ነው፡፡ ተራራማውና ሜዳማው የካራባኽ መሬት ግን በኢኮኖሚያዊና በባህላዊ መስክ ጥብቅ ቁርኝት ነበራቸው፡፡

ከእነዚህ ምንጮች በግለጽ እንደተቀመጠው የካራባኽ

ተራራማው የካራባኽ አካባቢ ገጽታ







እ.ኤ.አ በ18ኛው ክ/ዘ የካራባኽ አስተዳዳሪ በነበረው ፓናህ አሊ የተገነባው እና አሁን በአርሜኒያ ወታደሮች የተወረረው የሻኽቡላግ ቤተ-መንግስት



ግዛት ከአራዝ ወንዝ የሚጀምርና እስከ ሰሜናዊ ምዕራብ አቅጣጫ የተዘረጋ ከምስራቅ ባይላጋንና ከየጉሽታስፊ እስከ ዘጋምቻይ ጠረፍ ያለውን መሬት ያጠቃልላል፡፡ በ14ኛው ክ/ዘመን በደራሲ ሓምዱላህ ጋዝቪኒ ሪፖርት እንደተደደረገው ደግሞ የካራባኽ ድንበር እስከ አራዝ ወንዝ መስፋፋቱን ነው፡፡

እውነታው እንደሚያሳየው በሰሜን ጎይክቼ የምትገኝ ዘጋም እና ሁሉም በኦቶማን ኢምፓየር የነበሩ ግዛቶች /በይላጋን/ የካራባኽ ነበሩ፡፡ የካራባኽ አካባቢ ከሺርቫን በሚያወስነው እንዲሁም የካራባኽ የንግድ መስመሮች ከነበሩት ከኩራና አራዝ እስከ የትቢሊሲ ወንዞች መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ይህ ሁሉ የቦታ ስሞች ጥናት የሚያመላክተው ካራባኽ ና አራን ከጥንት ጀምሮ የሚያስተሳስራቸው የታሪክ ገመድ እንዳለ ነው።

የ14ኛው ክ/ዘመን ደራሲ ፋዝሉላህ ራሺድ አድ-ዲን ቀደም ሲል የተጠቀሰውን የረጋግጣል። ሙጋን፣ አራንና ሼኪ የካራባኽ ኽ ክልሎች ናቸው ብሏቸዋል፡፡ የራሺድ አድ-ዲን ስራ የካራባኽ ኽ ግዛትን በትክክል ለማመልከት ይረዳል፡፡ ጋፋን ከናክቺቫን ቱማን ክልል እንደምትመሳሰል እንዲሁም ናክቺቫን ቱማ በካራባኽ ድንበር ላይ የነበረች መሆኗን ግልፅ የሚያደርግ ነው፡፡ ይህም ከ13-14ኛ ክ/ዘመን የነበረው የካራባኽ ድንበር በደቡብ እስከ አራዝ ወንዝ፣ በደቡብ ምዕራብ እስከ ሃካሪ ወንዝ፣ በሰሜን ምዕራብ እስከ ዘጋምቻይ፣ በሰሜንና ሰሜን ምስራቅ የሺርቫን ግዛት እስከሆነው ኩራ ወንዝ እንዲሁም በደቡብ ምስራቅ እስከ ጉሽታስፊ ክልል እንዲሁም በተጨማሪ የካራባኽ አስተዳዳር ተራራዎችና ሜዳዎችን አዋህዳ የያዘች እንደነበረች ማስረጃ ነው፡፡

በ13ኛውና 14ኛው መቶ ክ/ዘመን ካራባኽ በአዛርባጃን ይካሄድ የነበረ ዋናው የማህበራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ማዕከል ነበረች፡፡ የሁላጊድና ጃላይሪድ ግዛቶች መሪዎች የሚያርፉበትና የሀገር ወሳኝ ጥያቄዎች የሚወሰኑበት በካራባኽ ነበር፡፡ ሞንጎላውያን መኳንንቶች ጋዛ ካንና አርፓ ካን ዙፋናቸው የጫኑባት እንዲሁም አርጉ ካንና አቡ ሰይድ የተባሉ መሪዎች ህይወታቸው ያለፈባትም /የሞቱባት/ ነበረች፡፡

ካራባኽ በሁላጊድ ጃላይሪድ ቤተሰቦች በሳቲበይ ካቱን እና ልጃቸው ሱርጋን፣ ሙሐመድበይ ጉሹ ቀጥጥር ስር ነበረች፡፡ እአአ በ1343 በሐጂ ሐምዛ፣ ሙላይድ፣ ሐሰን ቾባኒ ኢክታጂ እና ሑሴን አንቡጋ የሚመራ እንዲሁም እአአ በ1351 ሌላኛው በዳሉ ባያዚድ የሚመራ አመጽ በካራባኽ ተካሄዷል፡፡ እነዚህ ዓመጾች ችግር ያስከተሉ ቢሆንም በከፍተኛ ጥረት ተገትተዋል፡፡ የካራባኽ አካባቢ ባላባት በተለይ ጋዚ ሙኪ አድ ባርዳይ አንጻር የፊውዳላዊ አገዛዝ ጠበቃ ከነበረው ቾባንዲ ጋር በተደረገ ፀረ ፊውዳላዊ ስርዓት ጦርነት ትልቅ ሚና ነበረው፡፡ ሺርቫንሻህ ኪይ ካቩስ (1344-1372)፣ አለቃ



ሼክ ኡቬይስ ጃላይሪድ (1359 - 1374) እና ቀጥሎ ኢሚር ቲሙር (1370 – 1405) በካራባኽ ከፍተኛ ተፅእኖ መፍጠር የቻሉ ሰዎች ነበሩ፡፡

ከ12 እስከ 13ኛ መቶ ክ/ዘመን የካቸን አስተዳደር በካራባኽ ተራራማዎች ክፍል ነበር፡፡ የካቸን አስተዳደር በአራን ክልል የሚገኝ ቢሆንም ተራራማውና ደን የበዛበት ግዛት በመሆኑ ለመቆጣጠር አስቸጋሪ ነበር፡፡ ይህ ቦታ ትልቁ ምሽግ የስልጣኑ ዋና ማዕከልና የጦር መሳርያ ማከማቻ ነበር፡፡ የካቸን አስተዳር መፈጠር የጥንታዊት ሀገረ አልባኒያን ትንሽ ግዛት ዳግም ለመመስረት ነበር፡፡ የአስተዳደሩ ሰልጣን የአበበውም በዘመነ ሐሰን ጃላል (1215 – 1261) ‹‹የአልባኒያ ንጉስ››፣ ‹የአልባኒያ ድንበር ባለቤት› እና ‹የካቸንና የሀገረ አርትሳክ ንጉስ› በሚባልበት ወቅት ነበር፡፡ የሐሰን ጃላል ቤተሰብ ከትልቁ የአልባንያ ንጉስ መክራኒድ ስርወ መንግስት የመጣ ነው፡፡ ታዋቂውና ትምህርቱን በአርመኒያ የተማረው አይ ኤ ኦርቤሊ ካቸን ‹የጥንታዊት አልባንያ አካል› ነው ብሎ ያምናል፡፡ ስለዚህ የካቸን ስልጣኔና በተቀረጹ ማስረጃዎች ራሱ ‹የአልባንያ ንጉስ› ብሎ የሚጠራ መሪው ሐሰን ጃላል ከእውነታው በጣም በመራቅ ካቸን እንደ ‘የአርመን ግዛት’ አድርጎ የማቅረብ ዓላማ ነበረው፡፡

መቀመጫቸውን በሰሜናዊ አዛርባጃን አድርገው የነበሩት የካቸን መሪዎች በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መባቻ ላይ ለሞንጎልና ኮሪዝምሻክ ጃላል አድ ዲን (እአአ1200-1231) ለጥቃት ተጋለጡ፡፡ ይህንን ተከትሎም የካቸን ልዑል የነበረው ሀሰን ጃላል የሞንጎል ወታደራዊ መሪ ከነበረው ጁቺ ቡጋ ጋር ግንኙነት ጀመረ፡፡ በዚህም ወራሽነቱንና ስልጣኑን ማስከበር ቻለ፡፡ በኋላ ላይም እአአ በ1225 ከባቱ ካህን ልጅ ከሆነው ሳርታን ጋር በመሆን ሞንጎልያን ለመጎብኘት በሄደበት ወቅት በታላቁ ካህን ሜንጉ (እአአ ከ1251 እስከ 1260) ሞቅ ያለ አቀባበል ተደርጎለታል፡፡ ይህም ስልጣኑን ይበልጥ እንዲያጠናከር አስቻለው፡፡

ሀሰን ጃላል እአአ በ1261 በሞንጉል ልዑል በነበረው አርጉን ትዕዛዝ መሰረት ተገደለ፡፡ ከዚህ በኋላ ሞንጎሎች የሚቱ ሀሰን ጃላል ልጅ የሆነውንና እአአ እስከ 1287 የገዛውን ጃላል አታቤይን ገዥ አድርገው ሾሙት፡፡ በዚህ ወቅት ታዲያ የካቸን መሪዎች ህልውና አብቅቶ ነበር፡፡

ሰሜናዊ አዛርባጃንን ከደቡባዊ አዛርባጃን ከሚያገናኙት ድልድዮች መካከል አንዱ የሆነው እና አሁን በወራሪዎች ቁጥጥር ስር ሆኖ በከፊል የወደመው የ14ኛው ክ/ዘመኑ ሁዳፈሪን ድልድይ



በዚህ ወቅት የካራባኽ ህ ግዛት በስፋት የሚታወቅ ነበር፡፡ የመካከለኛው ዘመን የታሪክ ሊቅ የሆነው ሀምዱላህ ጋዝቪኒም ይሄንን ሀቅ በመጽሀፉ ላይ አረጋግጦታል፡፡ ይህ ታላቅ የታሪክ ሰው በመፅሀፉ ላይ ስለ ካራባኽ ህና አካባቢው ማለትም ኪይራክ፣ ባርዳና ሻምኪር እንዲሁም ስለ ጋንጃ ከተማ በስፋት ጽፏል፡፡ የኩራ እና አራዝ የመስኖ ውሃም የካራባኽ ህን ምድር ለምና ለእንስሳት እርባታም ምቹ እንዲሆንና ዛሬም ድረስ የካራባኽ  አካባቢ በዚህ እንዲታወቅ አድርገዋል፡፡

አውሮፓዊው ተጓዥ ጆን ሺልትበርገር በጉዞ መጽሀፉ ላይ፤ “በዓለም ላይ ምርጡ ሀር የሚመረተው በካራባኽ ነው” ሲል ምስክርነቱን ሰጥቷል፡፡ በዓለም ላይ እጅግ ትልቅ ፋይዳ ያላቸው የንግድ መስመሮችም ካራባኽ ን የሚያቋርጡ ናቸው፡፡ ከእነዚህም መካከል በሰሜን አቅጣጫ የሚጓዘውና ካራባኽ ን የሚያቋርጠው የሁልጋድ መስመር ተጠቃሽ ነው፡፡ ይህ መስመርም በጠቅላላው ከ280 እስከ 300 ኪሎ ሜትር እንደሚደርስ ይገመታል፡፡ የተለያዩ የእጅ ስራና የንግድ ማዕከሎችም በዚህ የንግድ መስመር ተቋቁመዋል፤ ከተሞች ተቆርቁረዋል፡፡ በተለይም እንደ ካህር፣ ጋርክ፣ ላምባራን፣ ባዛርጂክ፣ ባርዳ፣ ጁዝቡዝ፣ ዲኪ ኢስፋጋን፣ ክሃንጋ ሹቱር፣ ጋንጃ፣ ሻምኪር፣ ዩርት ሻዴክባን፣ አግስታፋ እና ያም ያሉ ታላላቅ የንግድ ማዕከሎች ተመስርተው እንደ ነበር ታሪክ ይነግረናል፡፡

ሌላው ጉዳይ በካራባኽ  ያለው የጎሳ ስብጥር ነው፡፡ ዜድ ኤም ቡኒያቶቭ የተባለ ምሁር እንዳስቀመጠው፤ የአራን ነዋሪዎች የቱርኪስ ቋንቋ ተናጋሪ ህዝቦች ነበሩ፡፡ የ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ስራዎች እንደሚያሳዩትም ከአራን ነዋሪዎች መካከል በአካባቢው ዋነኛ ጎሳ የነበረው የአጃኢብ አድ ዱንያ የቱርኪስ ሰዎች ግዛቱም በሙስሊሞች ስር እንደ ነበር ተጽፏል፡፡ በዚሁ ክፍለ ዘመን የተጻፉ ሌሎች የታሪክ









ድርሳናትም የአራን ሰዎች በአንድ ላይ ተሰባስበው በህብረት ይኖሩ እንደነበር ይናገራሉ፡፡

እንደሚታወቀው በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ በነበረው የሞንጎሎች ዘመቻ ወቅት ጥቂት የሞንጎል ታታር ጎሳዎች ካራባኽ ን ጨምሮ ወደ ተለያዩ የአዛርባጃን ግዛቶች በመግባት ሰፍረዋል፡፡ በተመሳሳይ የአልባንያ ጎሳ አባላት የሆኑ ሰዎችም በተራራማው የካራባኽ  አካባቢ በመስፈር የተለያዩ ቦታዎችን ይዘዋል፡፡

በረጅሙ የካራባኽ  ግዛት ታሪክ ውስጥ የአራን እና በአጠቃላይ የካውካሲያን አልባኒያን አካባቢ የእኛ ነው በሚል አርሜኒያዊያን እንግዳ የሆነ ጥያቄ ያነሳሉ፡፡ ከዚህ አንጻር በተለይ ከመካከለኛው ክፍለ ዘመን በኋላ ላለው ታሪክ በአርሜኒያ የተዘጋጀው ካርታ ትኩረትን የሳበ ነው፡፡ እአአ በ1982 በኤስ ጊ ይርሚአን አማካኝነት በአርሜኒያ ይርቫን ከተማ የታተመውና "**አርሜኒያና ጎረቤት አገራት ከ**701 **እስከ** 862" በሚል የታተመው ካርታ አርሜኒያኖች ምን ያህል የአዛርባጃንን ታሪክና ግዛት በመጻረር የይገባኛል ጥያቄ እንደሚያነሱ ያሳያል፡፡ በዚህ ካርታ መሰረትም የካውካሲያን አልባኒያ እንዲሁም ከጥቁር ባህር አካባቢ ያሉ የደቡብ ምስራቅ መሬቶች ብሎም ኡርሚያ ሀይቅ የአርሜኒያ ሆነው ይታያሉ፡፡ ይህ ቅጥፈት የተሞላበት ካርታ አረቦች የካውካሲያን አልባኒያን በተቆጣጠሩበት ወቅት መሬቱ ለአርሜኒያ ተሰጥቷል የሚል የሀሰት ታሪክ ለማጻፍ ያለመ ነው፡፡ እውነታው ግን አረቦች አካባቢውን በተቆጣጠሩበት ዘመን እነዚህ መሬቶች በአዘርባጃነ ግዛት ውስጥ የነበሩና በተመሰረተው እስላማዊ ግዛት ውስጥም አንድ አውራጃ ሆነው ተካተው መተዳደራቸው ነው፡፡

ይህ የአርሜኒያዎች የአዛርባጃንን መሬት ይገባናል የሚለው ቅጥፈት የተሞላበት አካሄድ በአረቦች ዘመንም ይሁን ዘግየት ብለው በ13ኛው እና 14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በራሳቸው በተሰሩ በርካታ ታሪካዊ ካርታዎች ላይም ተንጸባርቋል፡፡ ለአብነት ያህልም ቢ ኤ አሩታዩኒአን በተባለ አርሜያዊ የተሰራው ካርታ፤ ከሲቫስ እስከ ካራባኽ ያለውን የቱርክን መሬት በአርሜኒያ ግዛት ውስጥ አካቶት ይታያል፡፡ በጣም የሚገርመው ግን ካራባኽ  በዚህ ካርታ ውስጥ አለመካተቱ ነው፡፡ ይህ ሁሉ መረጃ የሚያሳየው



አርሜኒያ በካራባኽ ም ብቻ ሳይሆን በአራን ላይም ጭምር የሌላቸውን የግዛት ባለቤትነት በመካድ እውነት ለማስመሰል የፈጠሩትን የአፈታሪክ ድርደራ ነው፡፡

ሀምዱላህ ጋዝቪኒ በተባለ የታሪክ ሰው መረጃ መሰረት የአርመኖች ክልል ታላቁ አርሜኒያ እና ታናሹ አርሜኒያ በሚል በሁለት የተከፈለ ነበር፡፡ ታላቁ እርሜኒያ እንጂ ታናሹ አርሜኒያ ከኢራን ጋር አብሮ የተዋቀረ አልነበረም፡፡ ይልቁንም ድንበሩ የነበረው ይኸው ታናሹ አርሜኒያ የተባለው አካባቢ ነው፡፡ በዚህ ዘመን የነበሩ ሁሉም ማስረጃዎች የሚያሳዩት አርሜኒያዊያን የሚያነሱት የመሬት ይገባኛል ጥያቄ በውሸት ሰነድ ላይ የተመሰረተና ምንም አይነት እውነተኛ የታሪክ ማስረጃ የማይቀርበበት መሆኑን ነው፡፡

በአጠቃላይ አርሜኒያዊያን ለሚያነሱትና ከጥንት ጀምሮ የአዛርባጃን ግዛት አካል የነበረውን የመሬት ይገበኛል ጥያቄ ገለልተኛ የሆኑ ምንጮች ሳይቀሩ አጠንክረው ሀሰትነቱን አረጋግጠዋል፡፡ “ታላቁ” የሚለው ቅፅልም ቢሆን ከአዛርባጃን በስተምዕራብ የሚገኝ የአርሜኒያን አነስተኛ ክልል የሚያሳይና የአራን አካል መሆኑ ግልጽ ሆኗል፡፡

አርሜኒያዎች በዚህ አካባባ ከሚያነሱት የግዛት ይገባኛል ጥያቄ ጎን ለጎን የአራን ካራባኽ ህዝቦች አርሜኒያዊያን ናቸው የሚል የጎሳ አተያይ ያለው ጥያቄም ያቀርባሉ፡፡ እነዚህ አርሜኒያዊያንም በአካባቢው ያለውን ህዝብ መስርተዋል ሲሉ ሌላ ቅጥፈት ያስደምጣሉ፡፡ ለዚህ ቅጥፈታቸው ደግሞ የሚያቀርቡት ማስረጃ የአልባኒያዊያንን ባህል ነው፡፡ በካራባኽ የሚኖሩ አልባናዊያን ክርስቲያኖች መሆናቸውን በመመርኮዝ አርሜኒያዊያን ስለሆኑ ነው ክርስቲያን የሆኑት የሚል መከራከሪያ ያቀርባሉ፡፡ ይህ ሳይንሳዊ ያልሆነ መላምት ግን ፉርሽ የሚሆነው በራሳቸው በአልባናዊያን የታሪክ ጸሀፊ በሆነው የጋንድዛኩ ኪራኮስ የ12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ስራ ላይ ነው፡፡ በዚህ ስራ ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው የአልባኒያ ህዝቦች ከአርሜኒያዊያን የተለዩ ናቸው፡፡ አርሜኒየዊያን፣ ጆርጃዊያን፣ አግቫኖች እና አልባኒያ ከአርሜኒያን ጋር የተቀላቀሉ አይደሉም ይላል፡፡

በ13ኛው እና 14ኛው መቶ ክፈለ ዘመን ላይ ካራባኽ ን ጨምሮ በአካባቢው ያሉ ተራራዎችና ሜዳዎች በአራን ማዕከላዊ አካባቢ ውስጥ ይገኝ የነበረ ክልል ሲሆን፤ ይህ አካባቢ ከአርሜኒያ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት አልነበረውም፡፡ ክርስቲያን የሆኑት የክልሉ ህዝቦችም በስረ መሰረታቸው አልባናዊያን ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ሁሉም መረጃዎች የሚያሳዩት ለክፍለ ዘመናት የተጻፉ ሰነዶችም የሚመሰክሩትና በእኛም የተብራሩት ካራባኽ የአዛርባጃን ነፍስ መሆኑን ነው፡፡